## ሞትን . . .

ከገጽ ፩ የዞረ

ተሰን መስለን እንነሣለን እንጂ ሰውነ
ታችን በመንፈስ ቅዱስ ሳይታደስ
በብልየት አይደለም ቅዱስ ጳውሎስ
ሥጋችን እንደሚታደስ በአርአያ ክር
ስቶስ እንደሚነሣ ያስተምረናል "እኛ
አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም
ደግሞ የሚመጣ መድኀኒትን እርሱ
ንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠ
ባበቃለን ። እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ
ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር
ክብር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረ
ደውን ሥጋችንን ይለውጣል ። ፊልጵ
፫ ቁ ፳-፳፩ ክርስቶስ ሙታንን መቀ
ስቀሱ ስለ ራሱም ሞቶ እንደሚነሣ
አስቀድሞ መተንበዩና ያንንም በትን
ሣኤው ማረጋገጡ የባሕርይ አምላክ
ነቱን ያስረዳል ፩ቱም ወንጌላውያን
የክርስቶስን ትንሣኤ ዘግበዋል በ፬ቱም
ወንጌሎች ክርስቶስ በመስቀል ላይ
ተቸንክሮ ከሞተ በኋላ ከሙታን ተለ
ይቶ እንደተነሣ የመቃብሩም ድንጊያ
በመልአኩ ተንከባሎ መገኘቱን መቃ
ብሩ ባዶ መሆኑን ጠባቆችም ደቀ መዛ
ሙርቱም ማረጋገጣቸው ተጽፏል ።
በመጨረሻም ፈጣሪያችን የክብር
ትንሣኤ ለመነሳት ያብቃን አሜን ።

